## ሄፓታይተስ ቢ ምንድን ነው?

ሄፓታይተስ ቢ ጉበትን የሚያጠቃ ቫይረስ ነው። ሳይታከም ከቆየ፣ የጉበት መጎዳትን እና ካንሰርን ሊያስከትል ይችላል።

በአለም አቀፍ ደረጃ በግምት እስከ 296 ሚሊዮን ሰዎች ከሄፓታይተስ ቢ ጋር እየኖሩ ነው። አብዛኞቹ ይህን አያውቁም ምክንያቱም ህመም አይሰማቸውም ወይም የታመሙ አይመስሉም።

ሄፓታይተስ ቢ በተበከለ ደም ወይም በተወሰኑ የሰውነት ፈሳሾች ከሰው ወደ ሰው ይተላለፋል።

## ሄፓታይተስ ቢ እና እርግዝና

ነፍሰ ጡር ከሆኑ፣ እንደ ቅድመ ወሊድ እንክብካቤ አንዱ ክፍል የሄፓታይተስ ቢ የደም ምርመራ ማድረግ አለብዎት።

በበሽታው ከተያዙ ሄፓታይተስ ቢ ን በወሊድ ወቅት አዲስ ወደተወለደው ልጅ ሊያስተላልፉ ይችላሉ።

ነፍሰጡር ከሆኑ እና ሄፓታይተስ ቢ ካለብዎት፣ ኢንፌክሽኑን ለመከላከል ልጅዎ ከተወለደበት ቀን ጀምሮ የተወሰኑ ክትባቶችን ማድረግ ይችላል።



## ለበለጠ መረጃ፡-

**Centers for Disease Control and Prevention (CDC፣ የበሽታ መቆጣጠር እና መከላከል ማዕከላት)**
www.cdc.gov/hepatitis/hbv/

**ሄፓታይተስ ቢ እናቶች**
www.hepbmoms.org (እንግሊዘኛ)

HepBHub
doh.wa.gov/hepbhub

DOH 420-406 May 2022 Amharic

ይህን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለመጠየቅ፣ በ 1-800-525-0127 ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም የመስማት እክል ያለባቸው ደንበኞች፣ እባክዎ 711 (Washington Relay) ላይ ይደውሉ ወይም በ civil.rights@doh.wa.gov ኢሜይል ያድርጉ።

ምንጭ፡- CDC, Protect Your Baby for Life



# ሄፓታይተስ ቢ፡-

# ራስዎን እና ልጅዎን ለመጠበቅ ማወቅ ያለብዎት ነገር

Washington State Department of Health



## ሄፓታይተስ ቢ ለልጄ አደገኛ ነው?

ልጆች በሄፓታይተስ ቢ ሲያዙ፣ የእድሜ ልክ፣ ስር የሰደደ ኢንፌክሽን የመያዝ እድላቸው 90% ያህል ነው።

ሳይታከም ከቀረ፣ ስር የሰደደ ሄፓታይተስ ቢ ካለባቸው 4 ልጆች 1 እንደ የጉበት መጎዳት፣ ይጉበት በሽታ፣ ወይም የጉበት ካንሰር ያሉ አደገኛ የጉበት ችግሮች ይይዘዋል።

እንደ እድል ሆኖ፣ የሄፓታይተስ ቢ ኢንፌክሽንን በጣም አስተማማኝ እና ውጤታማ በሆነ ክትባት መከላከል ይቻላል።

## ልጅዎን ይጠብቁ እና ሄፓታይተስ ቢ ን ይከላከሉ

ልጅዎ በተወለደ በ 24 ሰአታት ውስጥ የመጀመሪያውን የሄፓታይተስ ቢ ክትባት ማግኘት አለበት።

ሄፓታይተስ ቢ ፖዘቲቭ ከሆኑ፣ ልጅዎ በተወለደ በ 12 ሰአታት ውስጥ የ ሄፓታይተስ ቢ ኢሚውን ግሎቡሊን (HBIG) ማግኘት አለበት።

ልጅዎን ከሄፓታይተስ ቢ ለመጠበቅ 3 የሄፓታይተስ ቢ ክትባቶች እና የ HBIG ክትባት ያስፈልጋቸዋል። ልጅዎ የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ከ 9-12 ወራት ልጅዎ እንዲመረመር ያድርጉ።

| ቀን | ሄፓታይተስ ቢ ካለባት ሴት የተወለደ ጨቅላ ህጻን መውሰድ ያለባቸው |
|---|---|
| **በወሊድ ጊዜ** | የሄፓታይተስ ቢ የወሊድ ክትባት እና ኢሚውን ግሎቡሊን (HBIG) |
| **1-2 ወራት** | 2ኛ የሄፓታይተስ ቢ ክትባት ዶዝ |
| **6 ወራት** | 3ኛ የሄፓታይተስ ቢ ክትባት ዶዝ |
| **9-12 ወራት** | ልጅዎ እንደተጠበቀ ለማረጋገጥ ይመርመሩ |

ልጅዎን የሚጠብቁበት ሌሎች መንገዶች እነዚህ ናቸው:-

- ሄፓታይተስ ቢ ኖሮብዎትም ልጅዎን ጡት ማጥባት ይችላሉ። መሰንጠቅ ወይም የጡት ጫፎች መድማት ካጋጠሙዎት ሃኪምዎን ያነጋግሩ፣ ጡት በሚያጠቡበት ጊዜ የሚረዱዎት ሌሎች አማራጮች አሉ።
- የሄፓታይተስ ቢ ክትባት መዝገብዎን ይያዙ እና ወደ ህክምና ጉብኝትዎ ይዘውት ይምጡ።
- የቤተሰብ አባሎችዎ የሄፓታይተስ ቢ ምርመራ እንዲያደርጉ እና እንዲከተቡ ያድርጉ።

## ሄፓታይተስ ቢ ከሌለብዎት

አሁንም ቢሆን ራስዎን እና ልጅዎን በአስተማማኝ እና ውጤታማ ክትባት መጠበቅ ይችላሉ። ክትትሉም ማጠናቀቅዎን ያረጋግጡ!

| ቀን | ጨቅላ ህጻናት መወሰድ ያለባቸው |
|---|---|
| **በወሊድ ጊዜ** | የሄፓታይተስ ቢ የወሊድ ክትባት |
| **1-2 ወራት** | 2ኛ የሄፓታይተስ ቢ ክትባት |
| **6 ወራት** | 3ኛ የሄፓታይተስ ቢ ክትባት |

## ሄፓታይተስ ቢ ካለብዎት ራስዎን ይጠብቁ

የጉበትዎን ጤና ለመፈተሽ እና ህክምና እንደሚያስፈልግዎት ለማየት ተጨማሪ ምርመራዎች ሊያስፈሉዎት ይችላል።

አንቲቫይራል የሚባሉት መድሃኒቶች፣ ሄፓታይተስ ቢ ያለባቸውን ብዙ ሰዎች ያክማሉ። ይሁን እንጂ፣ ህክምና የሚያስፈልገው ሁሉም ሰው አይደለም።

ማንኛውም አይነት የመድሃኒት ትዕዛዝ፣ ማሟያዎች፣ ወይም ቫይታሚኖች ከመውሰድዎ በፊት ሃኪም ይጠይቁ ምክንያቱም አንዳንድ መድሃኒቶች ጉበትን ሊጎዱ ይችላሉ።

እንዲሁም ከሄፓታይተስ ኤ ክትባት ሊጠቀሙ ይችላሉ። ኢንፌክሽንዎን ለመቆጣጠር ከወለዱ በኋላ ሃኪምዎን ማግኘትዎን ይቀጥሉ።